# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመብራት አገልግሎት አስተዳደር ባለስልጣን

## መመሪያ ቁጥር 165/2017

# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመንገድ ዳር የሚተከሉ የመብራት መሰረተ-ልማቶች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት የሚከፈል የካሳ ክፍያን ለመደንገግ የወጣ መመሪያ

የአዲስ አበባ ከተማ የመንገድ መብራት አገልግሎት በሽፋን፣ በዓይነትና በቴክኖሎጂ አጠቃቀም እያደገ መጥቷል፡፡ በመሆኑም ይህንን እያደገ የመጣውን የመንገድ መብረት አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ በህግና ስርአት መምራት አስፈላጊ ነዉ፡፡ መንግስት ለመሰረተ ልማት ዝርጋታ እና ጥገና ከፍተኛ እያወጣ ይገኛል፡፡ በመንገድ ዳር የሚተከሉ የመብራት መሰረተ-ልማቶች፤ ምሰሶዎች እና በምሰሶዎች የተገጠሙ ስክሪኖች፣ ሲሲቲቪ ካሜራዎች፣ የዋይፋይ መሣሪያዎች እና በአረንጓዴ ቦታዎች የተተከሉ ጌጣጌጥ መብራቶች፣ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች እና መስመሮች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት የካሳ ክፍያ ሥርዓት ተዘርግቶ ካልተመራ በሚደርሰዉ ጉዳት ምክንያት የሕብረተሰቡን መብትና ጥቅም እንዲሁም  የከተማችንን ገጽታ ሊጎዳ የሚችል በመሆኑና ለመተካትና ለመጠገን ሌላ ተጨማሪ ወጪ የሚጠይቅ ስለሆነ ፣ ጉዳት አድራሽዎች ለምትክ የንብረት ካሳ ክፍያ ማስከፈል በማስፈለጉ የአዲስ አበባ ከተማ የመብራት አገልግሎት አስተዳደር ባለስልጣን በአዋጅ 84/2016 አንቀፅ 16 ንዑስ አንቀፅ 2(ሥ) በደንብ ቁጥር 166/2016  አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው መመሠረት ይህንን መመሪያ  አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በመንገድ ዳር የሚተከሉ የመብራት መሰረተ-ልማቶች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት የሚከፈል የካሳ ክፍያን ለመደንገግ የወጣ መመሪያ ቁጥር 165/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1. "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤
2. "አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
3. "ባለስልጣን" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመብራት አገልግሎት አስተዳደር ባለስልጣን ነው፤
4. **"ቅርንጫፍ ጽ/ቤት"** ማለት ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመብራት አገልግሎት አስተዳደር ባለስልጣን ተጠሪ የሆኑ በየክ/ከተሞች የተቋቋሙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን የሚወክል ነው፤
5. **"የካሳ ክፍያ"** ማለት በመንገድ መብራት መሰረተ ልማት ላይ ጉዳት ያደረሰ ሰው የተጎዳውን የመብራት መሰረተ ልማት መልሶ ለመግዛት ወይም ለመጠገን የሚከፍለው ክፍያ ሲሆን የአገልግሎት ክፍያንም ያጠቃልላል፡፡

6. **"የህዝብ አገልግሎት"** ማለት መንግስታዊ ተቋማት በሕግ የተሰጣቸውን ኃላፊነትና ተልዕኮ ለመወጣት የሚፈለግባቸውን ድርሻ በብቃት መወጣት ያጠቃልላል፤

7. **"መንገድ"** ማለት በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ ዋና መንገዶች፣ መለስተኛ መንገዶች፣ መጋቢ መንገዶች፣ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች፣ የመንደር መንገዶች፣ ወይም የአደባባይ ዙሪያዎች፣ የመንገድ አካፋይ ደሴቶች፣ በመንገድ ግራና ቀኝ ያሉ የእግረኛ ወይም የብስክሌት ማስተላለፊያዎች፣ የባቡር ሀዲዶች፣ ድልድይ ወይም በከተማው መሪ ኘላን መሠረት ለመንገድነት የተያዘን ቦታ ይጨምራል፤

8. **"ዋና መንገድ"** ማለት በከተማው መሪ ኘላን ላይ ዋና መንገድ (PAS) ወይም ዋና መጋቢ መንገድ (SAS) ወይም ቀለበት መንገድ (RR) ተብሎ የተጠቀሰ መንገድ ነው፤

9. **"የውስጥ ለውስጥ መንገድ** /LS/" ማለት በከተማው መሪ ኘላን ላይ የዋና መንገድ (PAS) መጋቢ

መንገድ ነው፡፡

10. **"አደባባይ"** ማለት በመንገድ መሃል በትራፊክ መሸጋገሪያና ማዟዟሪያ የሚያገለግል ሆኖ ለተለያዩ ሀውልቶች፣ ቅርጻ- ቅርፆች፣ የውኃ ፋውንቴኖች ለእጽዋት መትከያ የተተወ አረንጓዴ ቦታ ነው፤

11. **"ምሰሶ"**፡- ማለት የኤሌክትሪክ ኃይል፣ መብራት፣ ስክሪን፣ ሲሲቲቪ ካሜራ እና የዋይፋይ ቁሶች ተሸካሚ ሆኖ በተለምዶ ፖል እየተባለ የሚጠራ ነው፤

12. **"የመብራት መሰረተ-ልማት"** ማለት በመንገድ ዳር የሚተከሉ በተተከሉ ምሰሶዎች ወይም በምሶሶዎች ላይ የሚገጠሙ ስክሪኖች፣ ሲሲቲቪ ካሜራዎች ፣ የዋይፋይ መሳሪያዎች የአረንረጓዴ ቦታዎች ጌጣጌጥ መብራቶች፣ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎችና መስመሮች እና መሰል ንብረቶችን የሚያጠቃልል ነው፡፡

13. **"የአገልግሎት ክፍያ"** ማለት የተጎዱ የመብራት መሰረተ ልማቶችን ወደ ነበሩበት ለመመለስ የሚከፈል የባለሙያ፣ የጉልበት፣ የተሽከርካሪ፣ የማሽነሪ እና የተለያዩ የአስተዳደራዊ ወጪዎችን የሚያተቃልል ክፍያ ነው፡፡

14. **"አዋጅ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 84/2016 ማለት ነው፤

15. **"ደንብ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመብራት አገልግሎት አስተዳደር ባለስልጣን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 166/2016 ማለት ነው፤

16. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

17. በዚህ መመሪያ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ይጨምራል።

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ የመብራት መሰረተ-ልማቶች ላይ ለሚደርስ ጉዳት የካሳ ክፍያ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## በመንገድ ዳር በተተለከሉ የመብራት መሠረተ ልማቶች ላይ የሚደርስ የጉዳት መጠን አወሳሰን እና የካሳ ክፍያ አፈጻጸም

4. **የጉዳት ዓይነትና መጠን መለየት**

   1) ጉዳት የደረሰበትን መንገድ መሠረተ ልማቶች የጉዳቱን አይነት፣ የጉዳቱ መጠን በብር ተተምኖ ልዩ የአካባቢ መጠሪያ ቦታው፣ ተገልጾ ለጉዳት አድራሹ በጽሑፍ ይደርሰዋል፡፡
   2) የጉዳት መጠን መረጃ የመሰብሰብና የማደራጀት ስራው በባለስልጣኑ ዋና መ/ቤት እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አማካኝነት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
   3) የተደራጀውን የጉዳት መጠን መረጃ መነሻ በማድረግ ለደረሰው ጉዳት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለመተካት እንዲያስችል ለጉዳት አድረሹ የመክፈያ የጊዜ ገደብ ተቀምጦ እንዲያውቀው ይደረጋል፡
   4) ጉዳት አድራሹ ጉዳቱን ካላመነ መረጃዎች እንዲጣራና እንዲጠናቀሩ በማድረግ ባለሥልጣኑ ጉዳዩን በፍትሐብሄር ክስ እንዲከፍል ለማድረግ ክሱንና ማስረጃዎቹን ለፍትህ ቢሮ ያስተላልፋል፡፡
   5) የባለስልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት እና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አጠቃላይ የጉዳት ካሳ ክፍያን ያስፈፅማሉ፡፡

5. **የካሳ ክፍያ ውሳኔ የሚሰጥበት ሁኔታ**

   1) ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የመንገድ ዳር መብራቶች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ለህዝብ ጥቅምና የአገልግሎት ቀጣይነትን ለማረጋገጥ ሲባል ጉዳት አድራሹ ተመሳሳይ የንብረቱን ወቅታዊ ዋጋን ታሳቢ በማድረግ የሚተካበትና የአገልግሎት ክፍያ ካሳ መጠን ይወስናል፤
   2) ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ላይ በተገለጸው መሰረት ሙሉ በሙሉ በብረት ፣በኮንክሪት ወይም በእንጨት የተተከሉ የመንገድ ላይ የመብራት ምሰሶዎች ለሚደርሰው ጉዳት የንብረቱን ወቅታዊ ዋጋን ታሳቢ በማድረግ የካሳ ክፍያ የሚያስከፍል ይሆናል፡፡
   3) በከተማው መንገድ ዳር በተተከሉ የመብራት መሰረተ ልማቶች ላየ ጉዳት ያደረሰ ሰው የመብራት መሰረተ ልማቶቹን የካሳ ክፍያ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 በተቀመጠው ስሌት መሰረት በአንድ ሳምንት ውስጥ እንዲከፍል ይደረጋል፤

4) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ የግል፣ የመንግስት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተለያዩ የመሠረተ ልማት በሚገነቡበት ወቅት በመንገድ መብራት መሰረተ ልማቶች ላይ በሚደርሰው ጉዳት የሚያደርሱ ከሆነ የካሳ ክፍያነውን በአንድ ወር ዉስጥ የሚያስከፍል ይሆናል፤

6. <u>የካሳ ክፍያ መጠን</u>

1) በመብራት መሰረተ ልማቶች ላይ ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ. ጉዳት ያደረሰበትን መሰረተ ልማት ወቅታዊ ዋጋ 100% ፤

ለ. ጉዳት የደረሰበትን መሰረተ ልማት መልሶ ለመትከል ወይም ለመጠገን የሚያስፈልገውን ሙሉ የአገልግሎት ክፍያ፤

ይከፍላል፡፡

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተቀመጠውን የካሳ ክፍያ የባለስልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት

እና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ያስፈፅማሉ፡፡

3) በመብራት መሰረተ ልማቶች ላይ ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀፅ ንዑስ

አንቀፅ 1 የተቀመጠውን የካሳ ክፍያ ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ ጉዳዩ በፍትሐብሔር

ክርክር እንዲደረግበት ለፍትሕ ቢሮ ይላካል፡፡

4) ጉዳት አድራሾች በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሠረት የካሳ ክፍያውን በአንድ ጊዜ ለመክፈል አቅም የሌላቸው ከሆነ ይህን የሚገልፅ ማስረጃ በ5 ቀን ውስጥ ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለባቸው፡፡

5) በዚህ አንቀፀ ንዑስ አንቀፅ መሰረት የሚያቀርቡትን ማስረጃ ባለስልጣኑ ከተቀበለው የአከፋፈል ሁኔታውን ይወስናል፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ከንኡስ አንቀጽ 1 እስከ 4 የተገለጹት ካሳ ክፍያን ማስፈጸም/ማስከፈል የሚቻለው በባለስልጣኑ እና በስሩ ባሉ የክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ይሆናሉ፡፡

7) በመንገድ ላይ መብራት መሰረተ ልማቶች ላይ ጉዳት ያደረሰ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ መሰረት የጉዳቱን ካሳ ለመክፈል ፍቃደኛ ካልሆነ ባለሥልጣኑ በፍርድ ቤት በፍትሐብሄር ክስ እንዲከፍል ለማድረግ ክሱንና ማስረጃዎቹን ለፍትህ ቢሮ ይልካል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ስለጉዳት አድራሾች ጥቆማ እና ክትትል

7. ስለጉዳት አድራሾች ጥቆማና ክትትል

በመንገድ ዳር የመብራት መሰረተ ልማት ላይ ለሚደርሰው ጉዳት የካሳ ክፍያን ተፈጻሚ ለማድረግ ስለጉዳት አድራሾች፡-

1) ከህብረተሰቡና ከተለያዩ ተቋማት በስልክ፣ በአካል፣ በተለያዩ ሶሻል ሚዲያዎች እና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ጥቆማውን ማግኘት ይቻላል፤
2) ባለስልጣኑ በመንገድ መብራት መሰረተ ልማት ጉዳት አድራሹን ለማግኘት በሚደረገው ክትትል ላይ ከህብረተሰቡ፣ ከፌደራል ፖሊስ እና ከአዲስ አበባ ፖሊስ፣ ከደንብ ማስከበር ባለስልጣን፣ ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን፣ ከአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን፣ ከአዲስ አበባ ኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ አርተፊሻል ኢንቴሊጀንሲ እና ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በቅንጅት በመስራት ይሆናል፤
3) በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) የተጠቀሱ አካላት በመንገድ ዳር በሚተከሉ የመብራት ምሰሰዎችና ምሰሶዎች ላይ የሚገጠሙ ስክሪኖች፣ ሲሲቲቪ ካሜራዎች፣ ዋይፋይ እና አረንረጓደ ቦታዎች መብራት፣መቆጣጠሪያ ጣቢያዎችና መስመሮች እና መሰል አገልግሎቶች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት በሕግ በተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነትን በቅንጅት በመስራት ይሆናል፤
4) በመብራት መሰረተ ልማት ለሚደርሰው ጉዳት በየአካባቢው ከሚገኙ የተለያዩ የማህበረሰብ አደረጃጀቶችና ባለድርሻ አካላቶች ጋር ባለስልጣኑ ተቀናጅቶ ይሰራል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የራሱን አደረጃጀት ይፈጥራል፤
5) የቅንጅት ስራውን የሚያስተባብር የባለስልጣኑ ኃላፊነት ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

8. ኃላፊነት

ማንኛውም አካል በማንኛውም ሁኔታ በመንገድ ዳር ላይ በሚተከሉ የመብራት መሰረተ ልማቶች ላይ  በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ጉዳት እንዲደርስ ማድረግ የለበትም።

9. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም በሚደረገው ማናቸውም እንቅስቃሴ ትብብር እንዲያደርግ ሲጠየቅ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

10. ማስፈጸሚያ ማንዋል ስለማውጣት

ባለስልጣኑ መመሪያው ለማስፈጸም የሚረዱ ማንዋሎችን ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡

11. ***መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ***

*ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በባለስልጣኑ ድህረ-ገፅ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡*

**አዲስ አበባ፣ የካቲት/2017 ዓ.ም**

ሰብስብ ሁሴን

***የመንገድ ዳር መብራት አገልግሎት አስተዳደር***

***ዋና ዳይሬክተር***